

# ሰው ሆይ !!

ምክሬን ልትሰማ፣ልብህን ክፈተው፣
ክፋት ምቀኝነት ለሚፈርሰው ገላ፣አፈር ለሚበላው፣
ትል ለሚመጠምጠው ፣ አንተ እንደጥላ ነገ ለምታልፈው፣
አንዴ አሸልበህ ፣ ለማትመለሰው፣
ክፋቱን ፣ ቅናቱን እርግፍ አርገህ ትተህ፣
ስንቅህን ሰንቀው ፣ ለወዲያኞው ቤትህ፣
ስንቅህን ሰንቀው ፣ ለወዳኛው ቤትህ ።
ይህ ነው የኔ ምክር፣ ከልብህ አድርገው፣
በምድር ሆዳም መሆን ፣ ለሰው ልጅ አይጠቅመው፣
ለደሃው ተሟገት፣ ሁሌ ለሚገፋው፣
ቤቱ ለሚፈርሰው፣ ለሚመዘበረው ፣
በጥይት ለሚያልቀው ፣ መኖርያ ለሌለው፣
ሁሌ ለሚያነባው ፣ ጎርፍ ለሆነው እንባው፣
አቤት የሚልበት ፣ መሄጃ ለሌለው፣
ከወንዝ ከገደል ዳር፣ በሜዳ ለሚያድረው፣
ለተገፋው ጭቁን ፣ ለተመዘበረው፣
ለፍትህ ቁምላት፣ ይህ መልካም ሥራ ነው።

መይሳው
ከምድረ ስዊድን
18-04-20